








# ከመጋረጃዉ ጀርባ

አዘጋጆች :- አብነት አሰፋ
ሳሙኤል አዳነ





# ከመጋረጃዉ ጀርባ

ይህ መፅሀፍ የተዘጋጀዉ አሁን በዘመናችን የመገለጥ መጨረሻ ተብለዉ እየተቆጠሩ ያሉ ፤ ነገር ግን መፅሀፍ ቅዱስ ፈፅሞ የማይደግፋቸዉ ፤ ይልቁንም በግልፅ ፊት ለፊት የሚቃወማቸዉን የሀሰት ትምህርቶች መነሻቸዉ ባዕድ አምልኮ እና ባዕድ ሃይማኖት እንደሆነ በግልፅ ለማሳየት ነዉ ።

በተለይም ደግሞ ሰዉ መንፈስ ነዉ ፣ ነፍስ አለዉ ፣ በስጋ ዉስጥ ያድራል የሚለዉ የስህተት ትምህርት ደሞ ለሌሎቹ የስህተት አስተምህሮቶች መነሻ ወይንም ደሞ መስፈንጠሪያ ሆኖ እንመለከታለን ።

የዚህ ትምህርት መነሻ ከሆኑት ባዕድ አምልኮዎች እና እሳቤዎች መሀከል ጥቂቱን ወስደን በዚህ መፅሀፍ ለመዳሰስ ሞክረናል ።

ያለንበት ወቅት መመርመርንና መጠየቅን የሚፈልግ ነዉ ። እንንቃ !!

ከአዘጋጆቹ !!!

# ማዉጫ

| ርዕስ | ገፅ |
| --- | --- |


ሰዉ መንፈስ ነዉ የሚለዉን ትምህርት የሚከተሉ ባዕድ አምልኮዎች ዝርዝር 4

የቃለ እምነት አስተምሮዎች ዝርዝር 5

ታዋቂ የሆኑ የቃለ -እምነት አስተማሪዎች የተናገሯቸዉ አደገኛ የምንፍቅና ንግግሮች 6

Mysticism ( ሚስጥራዊነት ) 10

New thought movement ( የአዲሱ አስተሳሰብ እንቅስቃሴ ) 10

Hinduism ( ሂንዱይዝም ) 12

Reincarnation ( ሪኢንካርኔሽን ) 14

LGBTQ ( ግብረ ሰዶም ) 15

🛑 #ሰው_መንፈስ_ነው የሚለውን ትምህርት የሚከተሉ ባዕድ ሃይማኖቶች ፣ ፍልስፍናዎች እና ልምምዶች 👇👇👇👇

1, Mysticism
2, New Thought Movement
3, Hinduism
4, Reincarnation
5, Gnosticism
6, Yoga Meditation
7, Mormonism
8, Quantum Physics
9, Plato's Theory
10, Greek Philosophy
11, Cult
12, Jainism
13, Shaktipat
14, Sikhism
15, LGBTQ+
16, Isha Kriya Meditation
17 , Kundalini Awakening
18, Astral Projection
19, Taoism
20, Korean Shamanism
21, Marcionism
22, Docetism
23, Pelagianism
24, Donatism
25, Simonianism
26, Daoism
27, Kejawen
28, Kabbalah
29, Cainites
30, Christian Science
31, British Israelism
32, Spiritualism
33, Scientology
34, Islamism Sufism
35, Meivazhi Religion
36, Alevism
37, Thelema

🔸 ከእነዚህም ☝☝ ውጪ ሌሎች ብዙ ሊኖሩ ይችላሉ

🔑 ሰዉ መንፈስ ነዉ የሚለዉን ትምህርት ጨምሮ ሌሎችንም የቃለ - እምነት ( Word of faith movement ) መነሻቸዉ ባዕድ ሀይማኖቶች ፣ ፍልስፍናዎች እና ልምምዶች ናቸዉ ።

🔶 የትምህርቶቹን መነሻ ቦታ ከማየታችን በፊት ትምህርቶቹን እንመልከት

❖ ሰዉ መንፈስ ነዉ ፣ ነፍስ አለዉ ፣ በስጋ ዉስጥ ያድራል ።

❖ እኛ የመለኮት ዘረመል ( DNA ) አለን ።

❖ የኢየሱስ እና የእኛ የአብ ልጅነት ተመሳሳይ ነዉ ።

❖ እኛ አማልክት ነን

❖ የክርስቶስ የመስቀል ሞት የሀጢያት ክፍያ መሆን አይችልም ።

❖ ክርስቶስ በመንፈስ ሞቶ በሲኦል ለሶስት ቀን በአጋንንት ተሰቃይቶ ዳግመኛ ተወልዷል ።

❖ እኛ ኃጢያት መስራት አንችልም ፤ነፍሳችንና ስጋችን ናቸዉ ኃጢያት የሚሰሩት ፤ መንፈሳችን አይረክስም ።

❖ እግዚአብሔር ሰዉን የፈጠረዉ እራሱን ለማራባት ነዉ ።

❖ እኛ ከአብ ዉስጥ ወተን መተናል ።

❖ ከአብ ጋር እኩል ነን ፣ ከኢየሱስ ጋር እኩል ነን ።

❖ ቃላችን የመፍጠር ሀይል አለዉ ።

## ➢ ታዋቂ የሆኑ የቃል - እምነት አስተማሪዎች የተናገሯቸዉ አደገኛ የምንፍቅና ንግግሮች :-



Kenneth copeland ( ኬኔት ኮፕላንድ )

" በኤደን ገነት የነበረዉ አዳም በሥጋ የተገለጠ እግዚአብሔር ነዉ ። "

🔶 ኬኔት ኮፕላንድ

" እግዚአብሔር አዳምን የፈጠረበት ምክኒያት እራሱን የማራባት ፍላግቱ ነዉ ። "

🔶 ኬኔት ኮፕላንድ

" እኔ ከእግዚአብሔር ጋር እኩል ነኝ .......... እኔ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር እኩል ነኝ ።

🔶 ኬኔት ኮፕላንድ

## 🔷 እኔ ከእግዚአብሔር ጋር እኩል ነኝ ።

🔶 Kenneth Copeland ( ኬኔት ኮፕላንድ )

### ይሄንን ለማለት የተጠቀመው ጥቅስ 👇👇

### ወደ ፊልጽስዩስ ሰዎች 2

------------

5፤ በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረ ይህ አሳብ በእናንተ ዘንድ ደግሞ ይሁን።

6፤ እርሱ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባ ነገር አልቈጠረውም፥

(KJV+Strong's)

------------

5 Let this mind be in you, which was also in Christ Jesus:

6 Who, being in the form of God, thought it not robbery to be equal with God:

🔑 " *ኢየሱስ ከአብ ጋር እኩል መሆኑን መቀማት እንደሚገባ አድርጎ አልቆጠረዉም ፤ በክርስቶስ የነበረ ሀሳብ በእናንተም ይሁን ስለሚል እኔም ከአብ ጋር እኩል መሆኔን እንደመቀማት መቁጠር አይገባኝም ። "* ብሎ ቃል በቃል ተናግሯል ።



Kenneth. E. Hagin ( ኬኔት ኢ. ሀገን )

" ... ከእግዚአብሔር ተለይቶ እኛ እንደነበርነው ሆኖ ነበር ፤ ምክንያቱም ስለ ሰው ሁሉ መንፈሳዊ ሞትን ቀምሶ ነበር ፤ እናም መንፈሱ የውስጠኛው ሰው ወደሲኦል ሄደ ፣ በእኔ ፈንታ ... አካላዊ ሞት ኃጢያታችሁን ማስወገድ አይችልም ፤ እርሱ ስለ ሰው ሁሉ ሞትን ቀመሰ ፤ መንፈሳዊ ሞትን ስለ መቅመስ ነው እያወራ ያለው ። ኢየሱስ የመጀመሪያው ዳግመኛ የተወለደ ሰው ነው ። "

🔶 ኬኔት ኢ. ሀገን




Chris Oyakhilome ( ክሪስ ኦያኪሎሜ )

" እኛ ከእግዚአብሔር ጋር በባህሪይ እና በመደብ እኩል ነን ።

🔶 ክሪስ ኦያኪሎሜ

⭕ ሰዉ መንፈስ ነዉ የሚለዉን ትምህርት የሚከተሉ ባዕድ ሃይማኖቶች ፣ ፍልስፍናዎች እና ልምምዶች ከዚህ በታች በዝርዝር ከነማብራሪያዉ ቀርቧል ።

## 1. Mysticism ( ሚስጥራዊነት )

📌 ልዩ በሆነ ወይንም በተለወጠ ንቃተ - ህሊና እና ከመለኮት ጋር አንድ የመሆን ስሜት የሚያምን የሃይማኖት እንቅስቃሴ ነዉ ።

📌 ይሄ አስተሳሰብ በሂንዱይዝም ፣በቡዲሂዝም እና በእስልምና ዉስጥ ያለ ሲሆን ወደ ክርስቲያኑ ማህበረሰብም መግባት ችሏል ።

📌 በዚህ እምነት መሰረት አካል የሰዉ ማንነት አይደለም ፤ የሰዉ እዉነተኛዉ እና ወሳኝ ማንነቱ መንፈሱ እንደሆነ ይታመናል ። በዚህ አስተሳሰብ ዉስጥ በመለኮት እና በሰዉ መሀከል ያለዉ ድንበር የደበዘዘ ነዉ ። በዚህ አስተሳሰብ ዉስጥ ያሉ ሰዎች እራሳቸዉን እንደመለኮት ክፍል ወይንም ከመለኮት ጋር አንድ አይነት እንደሆኑ አድርገዉ ይቆጥራሉ ። ይሄም ብዙ ጊዜ " Union with God " ወይንም " Divine Spark with in " ተብሎ ይገለፃል ። በዚህ እምነት መሰረት ሰዉ ከመለኮት የተነጠለ አምልኮ አቅራቢ ሳይሆን የመለኮት ቁራጭ ነዉ ።

📌 በ " Mysticism " ሥጋ የመለኮታዊዉ ማንነት ( መንፈስ ) ጊዜያዊ መኖሪያ እንደሆነም ይታመናል ። ይህ አስተሳሰብ " ሂንዱይዝም " በነበረበት ጊዜ እንኳን የነበረ እሳቤ ( Concept ) እንደሆነ ይነገራል ።

## 2. New thought movement ( የአዲሱ አስተሳሰብ እንቅስቃሴ )

እ.ኤ. አ 19ነኛዉ ክፍለ ዘመን በአሜሪካ ( USA ) የተጀመረ መንፈሳዊ እና ፍልስፍናዊ እንቅስቃሴ ነዉ ። ለአይምሮ ኃይል አፅንኦት ይሰጣል ፤ እንዲሁም ሰዎች መንገዳቸዉን ወደ ስኬታቸዉ እና ጤንነታቸዉ አድርገዉ በአይነ ህሊናቸዉ እንዲመለከቱ ያበረታታል ።

## የዚህ እንቅስቃሴ እምነቶች

- አዕምሮ በሽታን መፈወስ ይችላል ።
- አስተሳሰብ ፣ እምነት እና ንቃተ ህሊና እርስ በርሳቸዉ የተሳሰሩ እና ከአዕምሮ ያለፈ ተፅዕኖ ያላቸዉ ነገሮች ናቸዉ ።
- አዕምሮ የተሻለ ሕይወት የመኖር ሚስጥሮችን የመክፈት ሀይል አለዉ ።

🔖 **የዚህ እንቅስቃሴ አባት እንደሆነ የሚታመነዉ ግለሰብ " Phineas. P.Quimby ( ኩዉምቢ) ይባላል ።**

🔑 **በዚህ እንቅስቃሴ ዉስጥ " ሰዉ መንፈስ ነዉ " ማለት የሰዉ እዉነተኛ ማንነት መለኮት ፤ መንፈሳዊ ፍጡር ፣ በተለይ ደሞ የእግዚአብሔር አንድ ክፍል ነዉ ማለት ነዉ ።**

🔑 **በዚህ አስተሳሰብ መሠረት የሰዉ ዋና ማንነት <u>መለኮት እንጂ ቁሳዊ አካል አይደለም ።</u>**

## 🔍 የ " New thought movement " ቁልፍ ዕምነቶች ( ስለ ሰዉ )

- መለኮታዊ ማንነት = የሰዉ መንፈሳዊ ማንነት መለኮት ነዉ ።
- የሀሳብ የመፍጠር ጉልበት = ይሄ መንፈሳዊ ማንነት በሀሳብ ኃይል የራሱን እዉነት የመፍጠር አቅም አለዉ።
- " የክርስቶስ ንቃተ ሕሊና " ( Christ consciousness )

🔖 ወደ ክርስቶስ ንቃተ ህሊና መድረስ ዋና ግብ ተደርጎ ተወስዷል ፤ ይሄም የራስን መለኮታዊ ማንነት ሙሉ በሙሉ መረዳት ነዉ ።

🔖 Quimby ክርስቲያን ሳይንስ የሚባለዉ ቤተ - ክርስቲያን የመሠረተችዉ ማሪያም ቤከር ኤዲዲ ( 1821 - 1920 ) ላይም ከፍተኛ ተፅንኦ አሳድሯል ።

የአዲሱ አስተሳሰብ መሠረታዊ እምነት " ሰዉ እግዚአብሔር ነዉ ወይንም የእግዚአብሔር ክፍል ነዉ ፤ እናም መለኮታዊ ተፈጥሮዉን በሚገነዘብበት ጊዜ ወደ ክርስቶስ ንቃተ ሕሊና " Christ consciousness " ደረጃ ይደርሳል ። " የሚል ነዉ ።

የቃለ እምነት እንቅስቃሴም በ 19ነኛዉ ክፍለ ዘመን ከተነሳዉ የአዲስ አስተሳሰብ እንቅስቃሴ ጋር ግንኙነት አለዉ ። የ E. W. kenyon አስተምህሮም ከዚሁ እንቅስቃሴ የተቀዳ ነዉ ።

## 3. Hinduism [_ሂንዱይዝም ]

ሂንዱይዝም በአለም አቀፍ ደረጃ ከ 1 ቢሊዮን የሚበልጡ ተከታዮች ያሉት ጥንታዊ ሃይማኖት ነዉ ። አብዛኛዉ ምሁራን የሂንዱይዝም እምነት የጀመረዉ ከ 2300 - 1500 ዓ.ዓ ባለዉ ጊዜ መሀከል እንደነበረ ያምናሉ ። የተጀመረበት ቦታም ባሁኗ ፓኪስታን አቅራቢያ በኢንዱስ ሸለቆ ( Indus valley ) ዉስጥ ነዉ ። እንደ ሌሎቹ ሃይማኖቶች ሂንዱይዝም መስራች ግለሰብ የለዉም ፤ ከዚያ ይልቅ በዚያን ጊዜ የነበሩ ባህሎች ፣ እምነቶች እና ፍልስፍናዎች ለዚህ ሃይማኖት መነሻ ነበሩ ።

### የሂንዱይዝም ዋና ዋና እምነቶች

- ✓ **ብራህማን** = በየትኛዉም ቦታ እና በሁሉም ዉስጥ የሚገኝ አምላክ
- ✓ **ካርማ** = ሁሉም ተግባር መዘዝ እንዳለዉ የሚገልፅ የምክኒያት እና የዉጤት ህግ
- ✓ **ዳርማ** = ግለሰቦች ሟሟላት ያለባቸዉ የሞራል እና የስነ - ምግባር ተግባራት
- ✓ **ሞክሻ** = የነፍስ ከዉልደት ፣ ከሞት እና ድጋሚ ከመወለድ ዑደት ነፃ መዉጣት
- ✓ **የህይወት ዑደት** = መወለድ ፣ መሞት እና ድጋሚ መወለድ
- ✓ **የሚቀጥለዉ ሕይወት** = ሂንዱዎች ቀጣዩ ሕይወት ቀድሞ ከነበረዉ ሕይወት ዉስጥ በተኖረዉ ኑሮ ይመሰረታል ወይንም ይወሰናል ብለዉ ያምናሉ ።

🔒 በሂንዱይዝም " ሰዉ መንፈስ ነዉ " ተብሎ ይታመናል ፤ ይሄንንም " አትማን " ብለዉ ይጠሩታል። " አትማን " ዘላለማዊ የሆነን እዉነተኛ ማንነት ( True self ) ወይንም " መንፈስ " የሚገልፅ ቃል ነዉ ፤ ይሄም የአፅናፉ ዓለም ንቃተ ሕሊና ( ብራህማን ) አንድ ክፍል ተደርጎ ይታመናል ። በእምነቱም መሰረት " አትማን " ቁሳዊዉን አካል ሣይሆን በተለያዩ የሕይወት ኡደቶች ዉስጥ ድጋሚ ወደ አካል ዉስጥ በመግባት የሚጓዝ የማይሞት ማንነት ነዉ ።

🔒 *ሂንዱዎች የሕይወት ዓላማ በሁላችንም ዉስጥ ያለዉን መለኮትነት መፈለግና መገንዘብና መሆኑን ያምናሉ ። በእምነታቸዉም ዉስጥ ሰዉ መለኮታዊ መንፈስ ( Divine spirit ) እንደሆነ ይታመናል ። ይሄም " መለኮት መንፈስ " ከአፅናፈ ዓለሙ አምላክ ( ብራህማን ) ጋር አንድ የሆነ እና ተነጣጥሎ ሊታይ የማይችል እንደሆነ ያምናሉ ። የሂንዱ ህይወት ግብም ይሄንን መለኮታዊ ተፈጥሮ በመንፈሳዊ ልምምዶች እና እራስን በማወቅ መረዳት ነዉ ፤ ከዚያም ወደ ነፃነት ( ሞክሻ ) መድረስ ነዉ ።*

▣ "እኔ አካሌን አይደለሁም🙅‍♂️ ፣

እኔ አዕምሮዬን እንኳን አይደለሁም🙅‍♂️

... እኔ በቁሳዊ አካል ውስጥ የምኖር መንፈስ ነኝ"

➢ ከላይ ያሉት ንግግሮች meditation time ላይ ጥቅም ላይ የሚውሉ ናቸው ። ታዲያ meditation 🧘‍♂️ ስላችሁ መፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለውን አይደለም ፤ እያወራሁ ያለሁት ስለ Isha Kriya meditation (ኢሻ ክሪያ ሜዲቴሽን) ነው ፤ ይሄንን ያመጣው ግለሰብ ደግሞ ሳድጉሩ (Sadhguru) የሚባል Yogi እና mystic ነው ።

▫ ኢሻ ማለት "የፍጥረት ምንጭ" ማለት ሲሆን ክሪያ ደግሞ "ውስጣዊ ድርጊት" የሚል ትርጉም አለው ። ይሄ ሜዲቴሽን ከትንፋሽ ጋ የሚሠራ ሲሆን አየር ሲሳብ "እኔ አካሌን አይደለሁም" አየር ወደ ውጭ ሲወጣ ደግሞ "እኔ አዕምሮዬን እንኳን አይደለሁም" በማለት ይከናወናል ።

➢ ሰዎች ቁስ አካል ሳይሆኑ መናፍስት እንደሆኑ እንደ Bhagavad Gita ያሉ የህንድ ጥንታዊ ፅሑፎች ያስተምራሉ ። "እኔ አካሌን አይደለሁም ፣ እኔ አዕምሮዬንም አይደለሁም" የሚለው ነጥብ የ Bhagavad Gita ፍልስፍና ቁልፍ ነጥብ ነው ። Bhagavad Gita ገና በሁለተኛው ምዕራፍ ላይ ነው "እኔ ይሄንን አካል አይደለሁም" በሚለው ፅንሰ ሀሳብ የሚጀምረው ።

▣ Bhagavad Gita chapter 2

verse 19 = He who takes the Self to be the slayer  and he who thinks it is slain , neither of them knows . It doesn't slay nor is it slain .

verse 20 = it is not born , nor does it ever die ; after having been , it again doesn't cease to be ; unborn , eternal , changeless and ancient , it is not killed when the body is killed

verse 21 = whoever knows it to be indestructible , eternal , unborn and inexhaustible , how can that person slay . O Arjuna , or cause to be slain ?

verse 22 = Just as a man casts off worn out clothes and puts on new ones , so too the embodied Self casts off worn out bodies and enters others that are new .

➢ ከላይ ☝☝ እንዳየነው በ Bhagavad Gita ሁለተኛው ምዕራፍ ላይ ከአስራ ዘጠነኛው ቁጥር እስከ ሀያ ሁለተኛው ቁጥር ድረስ ክሪሽና ለአርጁና ሲናገር ያለውን ተመልከቱ 👇👇

ቁጥር 19 "እራስን እንደ ገዳይ የሚቆጥር ፤ ተገደለ ብሎ የሚያስብም ሁለቱም አያውቁም ። እራስ የሚገድልም የሚገደልም አይደለም"

ቁጥር 20 "አልተወለደም ፣ መቼም ደግሞ አይሞትም ፤ እየኖረ ያለ ሆኖ ፤ እንደገና ተመልሶ መኖር አያቆምም ፤ ያልተወለደ ፣ ዘላለማዊ ፣ የማይለወጥ እና ጥንታዊ ፣ አካል ሲገደል እርሱ አልተገደለም ።"

ቁጥር 21 "እራስ የማይጠፋ ፣ ዘላለማዊ ፣ ያልተወለደ እና የማይደክም እንደሆነ የሚያውቅ ሰው እንዴት ሊገድል ይችላል ፣ ኦ አርጁና ሊገደልስ ??"

ቁጥር 22 "ሰው ያረጀን ልብስ አውልቆ አዲሱን እንደሚለብስ ፤ በአካል ያለ እራስም ያረጁትን አካሎች አውልቆ ሌሎች አዳዲስ አካሎች ውስጥ ይገባል ።

▣ ከላይ እንዳያችሁት Bhagavad Gita የሚያስተምረው እራስ(self) ያልተወለደ ፣ የማይለዋወጥ እና የማይጠፋ እንደሆነ ነው ። በዚህ ትምህርት ውስጥ " እኔ አካሌን አይደለሁም " የሚለው ሀሳብ የመንፈሳዊ እውቀት መጀመሪያ እንደሆነ ይታመናል ። አካሉ የራሱ ማንነት እንደሆነ የሚያምን ሰው በዚህ አስተምህሮ መሠረት አላዋቂ እና መሃይም ነው ።

▣ የሂንዱይዝም እምነት ተከታዮች እና የ ሳድጉሩ ደቀመዛሙርት ዘወትር እንዲሁም ለሰዓታት ሜድቴሽን ላይ የሚጠቀሙትን ፅንሰ ሀሳብ የእኛው ጉዶች ፕሮቴስታንት "ሰባኪዎች" በመፅሐፍ ቅዱስ ጥቅስ አለባብሰው ፣ በተረት እና በምሳሌ አሸሞንሙነው ፣ በሃሌሉያ እና በእልልታ አሳጅበው ፣ በኪቦርድ እና በጩኸት አድምቀው ወደ መድረክ ማውጣታቸው በጣም አስገራሚ ክስተት ነው ። የሂንዱይዝም ቅርንጫፉ ሳይሆን ግንዱ ቤተክርስቲያን ውስጥ ገብቷል ።

▣ ወዳጄ "መንፈስ ነኝ ፣ አካሌን አይደለሁም" ብለህ የምታምን ከሆነ 99% አልልህም 100% ሂንዱይዝም 🧘🏽‍♀️ ገብቶሃል ። መፅሐፍ ቅዱስ ሳይሆን Bhagavad Gita "ተገልጦልሃል" ። ከሂንዱይዝም የመጣ ትምህርት እንዴት ሆኖ ነው የክርስትና ዋና መገለጥ የሚሆነው ብሎ መጠየቅ ያልቻለ ሰው አደጋ ላይ ነዉ ።

## 4. Reincarnation ( ሪኢንካርኔሽን )

በዚህ እሳቤ መሠረት " የሰዉ መንፈስ " ከሞት በኃላ ድጋሚ በሌላ አዲስ አካል ይወለዳል ። " Reincarnation የሚለዉ ቃል የመጣዉ " reincaratio " ከሚል የላቲን ቃል ሲሆን " እንደገና አካል መልበስ " ወይንም " ድጋሚ አካል ዉስጥ መግባት " የሚል ትርጉም አለዉ ።

በዚህ እሳቤ መሠረት አካል የመንፈስ ( የነፍስ ) መጓጓዣ ( Vehicle) ነዉ ፤መንፈስ ደሞ ሹፌሩ ነዉ ፤ አካል ሲሞት መንፈስ ወደ ሌላ አካል ይሸጋገራል ። ልክ አንድ ሰዉ በሕይወት ዘመኑ የተለያዩ መኪኖች ዉስጥ እንደሚጓዝ ሁሉ ነፍስ ( መንፈስ ) በኢያንዳንዱ " ሪኢንካርኔሽን " ዉስጥ የተለያዩ አካሎችን ታገኛለች ።

በዋናነት ይሄን እሳቤ የሚከተሉ ሃይማኖቶች የሚገኙት እስያ ዉስጥ ነዉ ። ለምሣሌ :- ሂንዱይዝም ፣ ሲኪሂዝም ፣ ጃኒዝም ፣ ቡዲዝም....... ወ.ዘ.ተ ። በዚህ እሳቤ ዉስጥ እያንዳንዱ ሰዉ ( ግለሰብ ) የመለኮት ክፍል እንደሆነ ይታመናል ፤ ማለትም በኢያንዳንዱ ሰዉ ዉስጥ የመለኮት ፍንጣሪ " Divine spark " እንዳለ ይታመናል ።

የዚህ አመለካከት አራማጆች የሚሏት ነገር አለች = " We are God with human experience "

🔖 በሪኢንካርኔሽን ፅንሰ - ሀሳብ ዉስጥ " ሰዉ በአካል ዉስጥ ያለ መንፈስ ነዉ " ማለት ብዙዉን ጊዜ " መንፈስ " ወይንም " ነፍስ " ተብሎ የሚጠራዉ የሰዉ ልጅ ዋና ማንነት በሥጋዊ አካል ላይ ብቻ ያልተገደበ እና ከሞት በኃላ መኖሩን የሚቀጥል ነዉ ማለት ነዉ ፤ ይህም መንፈስ በመሠረታዊነት በአዲስ ቅርፅ reincarnate በማድረግ ከዚያም በአዲስ ሕይወት ዉስጥ በአዲስ ቁሳዊ አካል ዉስጥ ይኖራል ።

## በዚህ ሀሳብ ላይ ያሉ ቁልፍ ነጥቦች

- ✓ **ዋናዉ ማንነት ( ተፈጥሮ ) መንፈስ ነዉ ።** = መንፈሱ እንደ እዉነተኛ ሰዉ ይቆጠራል ፤ ከሥጋዊ አካል የሚያልፍ ንቃተ - ሕሊና በሕይወታችን ዉስጥ ላሉ ልምዶቻችን እና እድገታችን ተጠያቂ ነዉ ።
- ✓ **የሪኢንካርኔሽን ዑደት** = አንድ ሰዉ ሲሞት መንፈሱ ከሥጋዉ ይወጣል ከዚያም በተለየ ጊዜና ቦታ በአዲስ አካል ይወለዳል ።
- ✓ **ካርማና ትምህርቶች** = ብዙ የሪኢንካርኔሽን እምነቶች በአንድ ህይወት ዉስጥ የተደረጉ ድርጊቶች እና ምርጫዎች የወደፊት ህይወት ሁኔታዎች ላይ ተፅዕኖ እንደሚያሳድሩ ይጠቁማሉ ። የካርማ ፅንሰ - ሀሳብ ነፍስ በሚቀጥለዉ ህይወት ዉስጥ የሚያጋጥማትን ልምዶች ይጠቀማል ።

## 5. LGBTQ+ ( ግብረ ሰዶም )

▣ LGBTQ+ 🌈 Vs Man is a spirit

🔸 #ሰው_መንፈስ_ነው የሚለው ትምህርት ግብረሰዶማዊነትን እንደሚደግፍ ያውቃሉ ?? ምናልባት ይሄንን ትምህርት የሚያስተምሩ ሰዎች ግብረሰዶማዊነትን ሲቃወሙ ሰምታችሁ ሊሆን ይችላል ፣ ትምህርታቸው ግን ግብረሰዶማዊያንን የሚያስደስት ትምህርት ነው ። እንዴት ?? መጀመሪያ ግብረሰዶማዊነት የተመሠረተበትን ፅንሰ ሀሳብ እንመልከት 👇👇

🔹 በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደምናየው ከእናቱ ማህፀን የሚወጣ ህፃን ወንድ ይሁን ሴት የሚለየው በሚወለድበት በዛው ሰዓት ነው ፣ ቀድሞ እግዚአብሔር ካልገለጠው በስተቀር ። በሀገራችን ባህልም ውስጥ የተወለደው ህፃን ወንድ ይሁን ሴት በተወለደበት ቀን የሚነገር መሆኑ የታወቀ ሐቅ ነው ። አሁን ላይ ደግሞ ገና በማህፀን ያለን ፅንስ በቴክኖሎጂ በመጠቀም ከመወለዱ በፊት ፆታውን መናገር ተችሏል ። እነዚህ ሁሉ እንደማስረጃ የሚጠቀሙት አካላዊ የሆነ ልዩነትን ነው ።

➧ ግብረሰዶማዊነትን የሚያቀነቅኑ ሰዎች ግን ይሄንን ይቃወማሉ ፣ "የትኛውም ህፃን በተወለደበት ቀን ፆታው ይሄ ነው መባል የለበትም እድጎ እራሱን ሲያውቅ ወንድ ወይም ሴት መሆኑን እራሱ ይናገር" በማለት ፆታ በውጫዊ ማንነት ሳይሆን በውስጣዊ ማንነት መገለፅ እንዳለበት ያስተምራሉ ።

➧ግብረሰዶማዊያን ህፃን ሲወለድ ፆታውን በውጫዊ ማንነቱ መግለፅ የለባችሁም ፣ ህፃኑ እራሱን አውቆ ፆታውን እስኪገልፅ መጠበቅ አለባችሁ የሚሉ ከሆነ እነርሱ ፆታውን ይገልፃል ብለው የሚያምኑት አካሉን ሳይሆን መንፈሱን ነው ። ሌላ ሰው ህፃኑ ሲወለድ ፆታውን መናገር የማይችል ከሆነ ሰው የሚያየው ውጫዊ ማንነትን ብቻ ስለሆነ የቀረው ግለሰቡ ብቻ የሚያውቀው ውስጣዊ ማንነት ወይም መንፈሱ ነው ። ግብረሰዶማዊያን እያሉ ያሉት እኮ "ፆታዬን የሚገልፀው ስወለድ አዋላጆች ያዩት አካሌ ሳይሆን ከእኔ ውጪ ማንም ሰው የማያውቀው መንፈሴ ነው" ነው ።

🔸 እንዴት ግብረሰዶማዊያን "በውጫዊ ማንነታችን አትግለፁን ውስጣችን ያለውን የምናውቅ እኛ ነን" ሊሉ ይችላሉ ለምትሉ ሰዎች እነዚህ ሰዎች በክርስቲያኑ ማህበረሰብ ውስጥ ያሉ መሆናቸውን ማስታወስ እፈልጋለሁ ፣ የራሳቸውንም መፅሐፍ ቅዱስ ማሳተም ችለዋል ።

🔹 1ኛ ቆሮንቶስ 2:11 ላይ "፤ በእርሱ ውስጥ ካለው ከሰው መንፈስ በቀር ለሰው ያለውን የሚያውቅ ሰው ማን ነው? ... " የሚለውን አስተውሉ ። አንድ ህፃን አድጎ ፆታውን እራሱ ይለይ ማለት ፆታው አካላዊ ሳይሆን መንፈሳዊ ነው እንደማለት ነው ። አንድን ወንድ መሆኑን የካደ ግብረሰዶማዊ "ይሄ አካል የአንተ ማንነት አይደለም" ብትሉት የሚቃወማችሁ ይመስላችኋል ?? ሰዎች ወንድ ለመሆኑ ማስረጃ አድርገው የሚያቀርቡለትን ውጫዊ ማንነቱን ማንነትህ አይደለም ስትሉት ውስጣዊ ማንነህ ነኝ ብሎ የሚያምነውን ነህ እያላችሁት አይደለምን ?? በእርግጠኝነት #ሰው_መንፈስ_ነው የሚለውን ትምህርት ግብረሰዶማዊያን በፍቅር ነው የሚከተሉት ፣ የሚፈልጉትን ይሰጣቸዋልና ።

🔸 ዘፍጥረት 1:27 ላይ እግዚአብሔር የፈጠረው መንፈስ ነው የሚሉ ሰዎች "ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው" የሚለውን ሐረግ ያላዩት ይመስላችኋል ?? #ኃይሉ_ዮሐንስ "መንፈስ ፆታ አለው ብዬ ነው ማምነው" ብሎ የተናገረውን አስታውሱ ። ሥጋ የሰው ማንነቱ ሳይሆን መኖሪያው ነው ከተባለ ዘፍጥረት 1:27 ላይ ወንድና ሴት ስለሆነ የተፈጠሩት መንፈስ የሆነው ግለሰብ ፆታ የሚገለፀው በግለሰቡ በራሱ እንጂ በመኖሪያው አይደለም ማለት የግድ ይሆናል ፤ ይሄ ደግሞ "የአንድ ሰው ፆታ ከሌላ ሰው የተሰወረ ነው የተወለደው ህፃን አድጎ እራሱን ሲያውቅ ይናገር" የሚለውን አመለካከት በግልፅ የሚያንፀባርቅ ነው ።

🔖 "፤ እንዲሁም ወንዶች ደግሞ ለባሕርያቸው የሚገባውን ሴቶችን መገናኘት ትተው እርስ በርሳቸው በፍትወታቸው ተቃጠሉ፤ ወንዶችም በወንዶች ነውር አድርገው በስሕተታቸው የሚገባውን ብድራት በራሳቸው ተቀበሉ።"
(ወደ ሮሜ ሰዎች 1: 27)

🔹 #ሰው_መንፈስ_ነው የሚለውን ትምህርት መቃወም #ግብረሰዶማዊነትን መቃወም ነው ። የ WOFM

Denomination ግብረሰዶማዊነትን መቃወም አይችልም ። አስተውሉ ፣ ከዚህ ምንፍቅና ጀርባ ብዙ አደገኛ እባቦች አድፍጠዋል ፣ ከእነዚህም አንዱ ግብረሰዶማዊነት ነው ።

🔸 በእግዚአብሔር ዘንድ እጅግ አስፀያፊ የሆነውን ግብረሰዶማዊነትን የሚደግፈውን አጋንንታዊ ትምህርት አጥብቀን መቃወም አለብን ፣ ፆታ መንፈሳዊ አይደለም ፣ የተገለጠ እና አካላዊ ተፈጥሮ ነው ። ሰው መንፈስ አይደለም ፣ መንፈስ ፆታ የለውምና ፣ ፆታም መንፈሳዊ አይደለምና ።

**ክርስቲያኖች ንቁ ፣ ተጠንቀቁ !!**

## Bible reporters ministry

## Yirgalem : Ethiopia

## April 2017

**Join us =** 🔷 **Do you know ? Channel on telegram**

🔷 **Bible reporters Channel on telegram**